በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ
እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ

# ግምገማ ትንበያ መጽሔት

## ከኖቬምበር 21-30/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

## እንዲሁም ከዲሴምበር 1-10 እና ከዲሴምበር 11-20/ 2024

## የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ዲሴምበር 2024

አዲስ አበባ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ርዕስ

እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ..... - 1 -

ምስል፡1 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች ..... - 2 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ..... - 4 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21 እስከ 30/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት ..... - 4 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ..... - 4 -

እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ..... - 5 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ..... - 5 -

እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ- 6 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ..... - 6 -

እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ..... - 7 -

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከዲሴምበር 1-10, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ..... - 8 -

ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11-20፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ..... - 9 -

እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ..... - 9 -

እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ..... - 10 -



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ


በኖቬምበር የሶስተኛዉ አሥር ቀናት ወደ ሀገራችን ሲገባ የነበረዉ ዕርጥበት አዘል አየር በመጀመሪያዎቹ ቀናቶች ላይ ከመጠናከሩ ጋር ተያይዞ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት ደቡብና ደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ ክፍሎች ላይ ዝናብ በቦታና በመጠን ረገድ የተሻለ ነበር፡፡ እንዲሁም ለዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች መጠናከር በማሣየታቸው ምክንያት በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከነበራቸው የደመና ሽፋን በመጠንም ሆነ በስርጭት የተሻለ ዝናብ የነበራቸው ሲሆን፤ በተለይም በዚህ ወቅት በመደበኛ ሁኔታ ደረቃማ የአየር ሁኔታ የሚስተዋልባቸዉ የሰሜን፣ የሰሜን ምስራቅ እና የምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ቀላለ መጠን ያለዉ ዝናብ በመጀመሪያዎቹ ቀናቶች ላይ ተስተውሏል፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከነበረዉ የደመና ክምችት የዝናቡ መጠንና ስርጭትም በተለያዩ ቦታዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ በአንዳንድ ስፍራዎች ላይ የተመዘገበ ሲሆን፤ በጥቂት ቦታዎች ላይም ከባድ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው አከባቢዎች ለመጥቀስ ያህልም በአቦምሳ 20.7፣ በአሊያ 49.1፣ በአማን 39.4፣ በባህር ዳር 54.2፣ በቦሬ 21.5፣ በቻግኒ 37.1፣ በጭራ 44፣ በዳንግላ 28.4፣ በደባርቅ 20.4፣ በደብረ ማርቆሰ 20.4፣ በጋቲራ 25.6፣ በጊዲ አያና 56.1፣28.7፣ በጎሬ 47.2፣ 31.3፣ በጭሮ 22.7፣ በጃራ 27.4፣ በጅግጅጋ 21፣ በጅማ 23.6፣ በኮንሶ 26.3፣ 42፣ 31.5፣ በሜኢሶ 21.9፣ በመተሃራ 75.8፣ በሞታ 34፣ በሞያሌ 24.4፣ በነቀምቴ 20.4፣ በኑራ ኤራ 51.9፣ በሻምቡ 22.5፣ እንዲሁም በቴፒ 29.7፣ 33.4 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡

በሌላ በኩል የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ እምብዛም ያልተጠናከረ ቢሆንም፤ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ለአብነትም በአምባ ማርያም 2፣ 3.6፣ 4፣ 4.2፣ 4.4፣ 4.4፣ 4.8፣ እና 4፣ በቡኢ 4.8፣ 4፣ 4.6 እና 4.6፣ በደብረ ብርሃን 3.8፣ 3.2፣ 3፣ 3.6፣ 3.2፣ 4.2፣ 3. 4፣ እና 3.2፣ በጅግጅጋ 2.4፣ 2.4፣ 4.3፣ አና 3.6፣ በመሀል ሜዳ 3.6፣ እና 3.2፣ በሮቤ 4.6፣ በሾላ ገበያ 2.1፣ 2፣ 2.1፣ 2.1፣ 2፣ 2፣ 1.2፣ 2.1፣ እና 2 እንዲሁም በወገል ጤና 4.5፣ በዲግሪ ሴልሽየስ ይገኙበታል፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በ26 የተለያዩ የሀገሪቱ ጣቢያዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ20 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው የዝናብ መጠን ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የሀገሪቱ ጣቢያዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 33.4 - 75.8 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካካል በመተሃራ፣ በጊዲ አያና፣ በባህር ዳር፣ በኑራ ኤራ፣ በአሊያ፣ በጎሬ፣ በጭራ እንዲሁም በኮንሶ ይጠቀሳሉ (ምስል 1) ፡፡




ምስል፡1 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በተለይም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት ከኦሮሚያ ክልል ጉጂና ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረናና ምስራቅ ቦረና፣ ባሌና ምስራቅ ባሌ፣ አርሲና ምዕራብ አርሲ፤ ከሶማሌ ክልል የሊበን፣ የዳዋ፣ አፍዴር፣ የሸበል፣ የነጎብ፣ የቆራሂ የዶሎ፣ የኤረር እና የጃረር ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጌዲኦ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ቡርጂ፣ ኮንሶ፣ አሊ እና ባስኬቶ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች ከ16-80 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ1-9 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸው:: በተጨማሪም



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


ከክረምት ወቅት ጀምሮ ዝናብ እያገኙ የነበሩት የሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፤ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ቄለም ወለጋ፣ ጅማ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የምዕራብ፣ የደቡብ፣ የማዕከላዊና የሰሜን ጎንደር፣ የአዊ ዞን፣ ምዕራብ፣ ምስራቅና ሰሜን ጎጃም፤ የሰሜን ምዕራብና የምዕራብ ትግራይ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የመተከል፣ የአሶሳ፣ የካማሺ እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር፣ አኝዋክ እና ማዣንግ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች ላይ ከ16-60 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ3-6 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸው፡፡

በሌላ በኩል የበጋ ዝናብ ተጠቃሚ ባልሆኑት አከባቢዎች ማለትም በደቡብ፣ በደቡብ ምስራቅ፣ በምስራቅና በመካከለኛዉ ትግራይ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የደቡብ ወሎ እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ የዋግህምራ ዞን፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ የማሂ፣ ጋቢ፣ ሃዉሲ እና ሃሪ ዞኖች ላይ ከ6-15 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ1-3 ቀናት ያህል ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ተመዝግቧል (ካርታ 1 እና 2) ፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት ከኦሮሚያ ክልል ጉጂና ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረናና ምስራቅ ቦረና፣ ከሶማሌ ክልል የሊበን፣ የዳዋ፣ አፍዴር፣ የሸበል፣ የቆራሄ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌዲኦ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ቡርጂ፣ ኮንሶ፣ አሊ እና ባስኬቶ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 3)፡፡ በተጨማሪም ከክረምት ወቅት ጀምሮ ዝናብ እያገኙ የነበሩት የሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፤ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ቄለም ወለጋ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የምዕራብ፣ የደቡብ፣ የአዊ ዞን፣ ምዕራብ ጎጃም፤ የሰሜን ምዕራብና የደቡብ ምስራቅ እና ምስራቅትግራይ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የመተከል፣ የአሶሳ፣ የካማሺ እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር፣ አኝዋክ እና ማዣንግ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 3) ፡፡




ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 1 ኢ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ





ካርታ 2 ኢ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21 እስከ 30/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ካርታ 3 ኢ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ሦስተኛዉ አሥር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ ተስተውሏል። ይህም ሁኔታ የመኸር ሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ለማከናወን አመቺ ነበረ፡፡ በሌላ በኩል በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ እና በደቡብ ምራብ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የነበረው እርጥበት ሙሉ በሙሉ እድገታቸውን ላልጨረሱ ሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንጻር አዎንታዊ ሚና የነበረው ቢሆነም በመደበኛ ሁኔታ ደረቃማ የአየር ሁኔታ በሚስተዋልባቸዉ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች የነበረው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በተለይም በደረሱ እና በመሰብሰብ ላይ በሚገኙ ሰብሎች አሉታዊ ተጽዕኖ ነበረው፡፡ በአንጻሩም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት ደቡባዊ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረዉ እርጥበት በበጋ ወቅት ለተዘሩ ሰብሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም በቆላማው አካባቢ ለሚኖሩት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሣርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት የጎላ ጠቀሜታ ነበረው ( ካርታ 4)፡፡





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21 እስከ 30/2024
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የኖቬምበር ሶስተኛ አስር ቀናት የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ የነበረው ተፅዕኖ ስንመለከት በመከከለኛው እና ታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ ተከዜ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌ ዳዋ፣ በላይኛው እና መካከለኛው ባሮ አኮቦ፣ አባይ በጥቂት በላይኛው እና መካከለኛ አዋሽ እንዲሁም በአብዛኛው ዋቢ ሸበሌ እና ኦጋደን ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ ከፍተኛ እርጥረበት ነበራቸው፡፡ በተለይም በለይኛው ባሮ አኮቦ፣ በታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ በጥቂት በላይኛው እና መካከለኛ አባይ እና በጥቂት መካከለኛው ተከዜ ተፋሰሶች ላይ በጣም ከፍተኛ እርጥበት ነበራው፡፡ የነበረው እርጥበት ለሰው ሰራሽም ሆነ የተፈጥሮ የውሃ መጠራቀምያዎች የውሃ ይዘታቸው በማሻሻል እረገድ ጠቀሜታው የጎላ ነበር፡፡ በሌላ በኩል በአብዛኛው አዋሽ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ኦጋዴን፣ አፋር ደናክል፣ የላይኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ተከዜ፣ ገናሌ ዳዋ የታችኛው አባይ እና ባሮ አኮቦ ተፋሰሶች ለይ ደረቅ ሁኔታ ስር ነበሩ (ካርታ 5)፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ


በሚቀጥሉት ቀናት ዝናብ ሰጭ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ እና የደቡብ ምስራቅ፣ እንዲሁም በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች በተለይም በመጀመሪያዎቹ ቀናቶች ላይ የተሻለ ገጽታ ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የቦረናና ጉጂ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች እና የሶማሌ ክልል ደቡባዊ ዞኖች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6)፡፡ በተጨማሪም በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ዝናቡ ቀጣይነት ይኖረዋል (ካርታ 6)፡፡

በአጠቃላይ ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት ከኦሮሚያ ክልል ጉጂና ምዕራብ ጉጂ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ቦረና እና ምስራቅ ቦረና ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጋሞ፣ ኮንሶ፣ ጌድኦ፣ ባስኬቶ፣ ጎፋ፣ ደቡብ ኦሞ፤ አሌ፤ በአማሮ እና ቡርጂ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበል፣ ኖጎብ፣ ቆራሂና ዶሎ ዞኖች በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6) ፡፡

በሌላ በኩል በፀኃይ ሀይል ታግዞ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ከአማራ ክልል በሰሜንና በደቡብ ጎንደር፣ በሰሜን፣ በምዕራብና በምስራቅ ጎጃም፣ በባህርዳር ዙሪያ እና በአዊ ዞኖች፣ ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ ዋግህምራ፤ ከትግራይ ክልል የሰሜን ምዕራብ፤የምዕራብ፣ የደቡብና የደቡብ ምስራቅና ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል በምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮጉዱሩ ወለጋ፣ በምዕራብና ቄለም ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፤ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል መተከል፣ አሶሳ፣ ካማሺ እና የማኦኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር እና አኝዋክ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮና ዳዉሮ፤ ማጀንግ ዞን፤ ከአፋር ክልል ቀለበቲ፣ ፋንቲ እና ሃሪ ዞኖች በተለይም በመጀመሪያዎቹ ቀናቶች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6)፡፡ ስለሆነም በሚኖሩት ደረቅ ቀናቶች የደረሱ ሰብሎች መሰብሰብ አስፈላጊ መሆኑን የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ይጠቁማል፡፡



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et





ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከዲሴምበር 1-10, 2024
የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በሚቀጥሉት የዲሴምብር ሁለተኛዉ አሥር ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ለዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች እንደሚቀጥሉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 7)፡፡ በተጨማሪም በደቡብ ምዕራብ እና በምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ቀላል መጥን ያለዉ ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 7)፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በተለይም በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል (ካርታ 7)፡፡ በሌላ በኩል በምስራቅ፤ በሰሜን ምስራቅ፣ በሰሜን እና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ወቅቱን ያልጠበቀ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 7)፡፡



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11-20፣ 2024

የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የመጀመሪያዎቹ የዲሴምበር አሥር ቀናት በአብዛኞቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚኖረው ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ የመኸር ሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ለማከናወን አመቺ እንደሚሆን ይጠበቃል። በሌላ በኩል አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት በተለይም በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ እና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ ኢጋማሽ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የሚጠበቀው እርጥበት ባሳለፈናቸው የበጋ ወራት በተለይም በደቡብ ኦሮሚያ አካባቢዎች ላይ ለተዘሩ ሰብሎች አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል። በተጨማሪም የእርጥበት ሁኔታው በአርብቶ አደርና በከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት በጎ ጎን ይኖረዋል፡፡ በሌላም በኩል ከሳምንቱ ኢጋማሽ በኋላ በተለይም በሰሜን፣ በሰሜን ምዕራብ እና በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ወቅቱን



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ያልጠበቀ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት ይጠበቃል። በመሆኑም አርሶ አደሮች ይህንኑ በመረዳት ሳይዘናጉ በማሳ ላይ የሚገኙና የደረሱ ሰብሎችን ባሉት ደረቅ ሰሞናት መሰብሰብ እንደሚያስፈልግ የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ይጠቁማል፡፡

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የዲሴምበር የመጀመርያዎቹ አሥር ቀናት አብዛኛውዎቹ የበጋ ወቅት እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑት የታችኛው ገናሌ ዳዋ፣ ዋቤ ሸበሌ እንዲሁም ኦጋዴን መጠነኛ እርጥበት ያገኛሉ። በተጨማሪም አብዛኛው የባሮ አኮቦ፣ የመካከለኛው እና የታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ አባይ፣ የታችኛው ተከዜ፣ ገናሌ ዳዋ፣ እና የላይኛው ዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት ያገኛሉ፡፡ ይህ ሁኔታ የገፀምድር የውሃ ሀብትን በመጠኑ እንደሚያሻሽል ይጠበቃል። በተለይም አብዛኛዎቹ ግድቦች አሁናዊ የውሃ መጠናቸው ከመደበኛው የተቀራረበ እና በተወሰኑት ላይ ከፍ ያለ በመሆኑ በቀጣይ የሚጠበቀው እርጥበት ለሀይል ማመንጫም ሆነ ለበጋ መስኖ ውሃ አቅርቦት አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል። በመሆኑም የሚመለከታችው አካላት በተለይም በእርጥበት አጠር አካባቢዎች አካባቢ የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች የውሃ ማሰባሰብ ስራዎችን ማከናወን ያስፈልጋል። በአንጻሩ አብዛኛዉ አዋሽ፣ አፋር ደናክል የላይኛው እና የመካከለኛ ተከዜ ተፋሰሶች በደረቅ የእርጥበት ሁኔታ ስር ሆነው ይቆያሉ፡፡



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et